# PANORAMA # XIII

## የትዝብት አድማስ

የካቲት 7 2000 ዓም

### አ! ሥልጣኔ በስምሽ ስንት ወንጀል ተፈፀመ ?

የምንኖረባት ዓለም የሕይወት ዘመኗን መቁጠር ከጀመረችበት አንስቶ እስከአሁን እስካለንበት ወቅት ድረስ በማር በተለወሱ ቃላትና መፈክር የተለያዩ በደሎችና ግፎች የተፈጸመባት ለመሆኑ በበርካታ ስንክሳሮች ተጽፈው እናገኛለን፡፡ በሃይማኖት÷ በሥልጣኔ÷ በዴሞክራሲና በሶሻሊዝም ሳቢያ÷ የተካሄዱት ጦርነቶች÷ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በበርካታ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦችን ጨፍጭፈዋል፡፡ ግፎች በደሎች ተፈፅመዋል፡፡ የጦርነቶቹ ሰለባ የሆኑት የዓለም ሕዝቦች ተዘርዝሮ የማያልቅ አረመኒያዊ ግድያ ተካሂዶባቸዋል፡፡ የቆየው ታሪካቸው÷ ባህላቸው÷ ቋንቋቸው÷ ዕምነታቸውና ዝርያቸው ጠፍቷል፡፡ ስብዕናቸው ከምድረ ገፅ ወድሟል፡፡ ዳር ድንበራቸው ተበውዟል÷ ተመሰቃቅሏል፡፡ ምዕራባውያን የአፍሪካን÷ የእስያንና የደቡብ አሜሪካን ሀገሮች ቅኝ ግዛት ለማድረግ የተጠቀሙበት ምክንያት÷ ያልሠለጠነውን ሕዝብ ለማሰልጠን÷በጨለማ የሚኖረውን ብርሃን ለመስጠት÷ አረማውያንን ለማጥመቅና የገነትን ጎዳና ለማሳየት የሚል ነበር፡፡ የአፍሪካን ሕዝቦች ወደገነት የሚወስዳቸው ሃይማኖት እንሰብካለን ባሉት ልሳናቸው በድርጊት የፈፀሙት ግን በባርነት ጎዳና ለባርነት ስቃይ ለመሆኑ ማንም አሌ የሚለው አይደለም፡፡ የኢጣሊያን ፋሽስቶች አለቃ የነበረው ቬኒቶ ሙሶሊኒ እንኳን በአቅሙ÷ ሀገራችንን በ1928 ዓም ለመውረር የተጠቀመበት ፕሮፓጋንዳ ፡ የገነት አመሳያ በሆነችው በአቢሲንያ የሚኖሩትን ያልሠለጠኑ ፍጥረቶችን አውጥቶ ሀገሪቱን የሰዎች መኖሪያ ለማድረግ ነው ብሎ የኢጣሊያንን ሕዝብ በማታለል ነው፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ በወቅቱ የሮማው ፓፓስ የነበሩት ሰው የሞሱሊኒን ጦርነት በመደገፍ ወራሪውን የፋሽስት ሠራዊት መርቀውና ባርከው ወደ ኢትዮጵያ መላካቸው ነበር፡፡ ይህ ፓፓስ አፈሩ ይቅለላቸውና ቡራኪያቸውን ለመስጠት ምክንያት የሰጡት ለሰላም ሲሉ እንደነበር÷ የታሪክ መዛግብት አሁንም በገፆቻቸው ውስጥ አቆይተውታል፡፡ እነኝህ ሁለት ኢጣሊያውያን የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች በወቅቱ ያልተገነዘቡት ታሪካዊ ሐቅ ቢኖር÷ መላው አውሮጳ በአምልኮ ጣዖት ሲያምን÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስትናን ተቀብሎ መኖሩን ነበር፡፡

በማር የተለወሰ ዕሬትና መርዝ በመርጨት ዓላማቸውን ከግብ ማድረስ የቅኝ ገዥዎች ስልትና ዘዴ የነበረ በመሆኑ በሦስተኛው ዓለም በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ የፈፀሙት ወንጀል ባያስደንቅም÷ የእነርሱ ሰበብ እስካሁንም መልኩን እየለዋወጠ መቀጠሉ ግን የሚያሳዝንና የሚያስቆጭ ክስተት እየሆነ መሄዱ ገሀድ ነው፡፡ በዘመናት የብዝበዛና ዝርፊያ መንገዳቸውን በመለዋወጥ በተለይም በአፍሪካ አህጉር የሚያደርጉት ጥቃት አሁንም እንደወትሮው እየቀጠለ

በመሄድ ላይ ይገኛል። ምንም እንኳ የአፍሪካ ሕዝቦች ከአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ባርነት የተላቀቁበት ወቅት ከአምሳ ዓመታት በላይ የሆነ ዘመን ቢያስቆጥርም፥ አሁንም ዕውነተኛ ነፃነታቸውን ተጎናጽፈዋል ማለት አይደለም። በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች አሁንም በእጅ አዙር የቅኝ አገዛዝ ስር እንደሚኖሩ መካድ አይቻልም። ሀገር በቀል አምባገነኖች በየሀገሩ በማስቀመጥ የምዕራባውያንን ጥቅም አስጠባቂ በመሆናቸው የሕዝባቸው ቀንደኛ ጠላቶች ሆነዋል። የኸም የሆነበት ምክንያት፥ የጥንቱ ቅኝ አገዛዝ በአዳዲስና መልኩን በሚለዋውጥ የምዕራባውያን የተራቀቀ ቅኝ ግዛት ሥርዓት እየተተካ በሄድ ላይ በመሆኑ ነው። የዛሬው  የቅኝ ግዛት ወረራ እንደ ጥንቱ  በይፋ ጦር አውጆ፥ ወታደር አዝምቶ፥ ውጊያ ከፍቶ በመዋጋት ሳይሆን፥  ለሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ተስማሚ ነው ብሎ በሚያምንበት አዳዲስ ብለሃትና ዘዴ ሆኗል።

የጥንቱ የቅኝ ግዛት ወረራ ግንባር ቀደም ሂደትና አፈጻጸም የሚካሄደው፥ ወንጌልን እንሰብካለን በሚሉ ሚሲዮናውያን፥ ሀገር እናስሳለን በሚሉ ሰላዮችና የሥነ ፍጥረት ተመራማሪዎችነን ባዮች ቡድኖች ነበር። የሁሉም ተልዕኮና ዓላማ ለቅኝ ግዛት ወረራ አመች የሆኑ ግንባር ቀደም መሰናዶዎችን ማመቻቸት ሲሆን፥ ዕውነተኛ የተኩላ ባኅርይና ማንነታቸውን የሚሸፍኑበት ግን የበግ ለምድ በመልበስ ነበር። ታዲያ ሁሉም በሃይማኖት ስም፥ በሥልጣኔ ሰበብ፥ በሸቀጣ ሸቀጥ ሳቢያ ለየሀገራቸው መንግሥታት የቅኝ ግዛትን ዓላማ በፋና ወጊነት መፈፀም ነበር። በአሁኑ ጊዜ ይህ ሁሉ ድካምና ልፋት የለም። ለሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት የሚስማማ አዳዲስ ብልሃትና ዘዴ እንደ አስፈላጊነቱ በተግባር በመለወጥ ላይ ነው።

ትላንት በሃይማኖትና በሥልጣኔ  ስም ያ ሁሉ ግፍ እንዳልተፈፀመ ሁሉ፥ ዛሬ ደግሞ በዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት ስም፥ይህ ነው የማይባል ግፍና በደል በመፈፀም ላይ ይገኛል።  ዛሬ፥ ምዕራባውያን የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ውጣ ውረድ ይህንን የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅና ለመከላከል ሽብርተኛን የሚያጠፉ ሳይሆን፥ በየቦታው አሸባሪን በመፈልፈል ላይ ይገኛሉ። ይህንንም ለማድረግ በሚወስዱት የኃይል ርምጃና የጥቃት ምት የሚተባበርላቸውና ትዕዛዛቸውንም የሚፈፅምላቸው አገልጋይ ይፈልጋሉ። ለዚህም እንዲያመቻቸው በየቦታው ያሉትን አሸባሪና አምበገነን መሪዎችን ያስታጥቃሉ፥ ያሰለጥናሉ። የገንዘብ፥ የዲፕሎማቲክና የፕሮፓጋንዳ ዕርዳታም በገፍ ይሰጣሉ። ለዚህ ሁኔታ እንደ ጉልህ ማስረጃ የሚጠቀሰው፥ በምዕራባውያንና በወያኔ መሪዎች መካከል የሚደረገው ትብብር ነው። ስለሌሎች አምባገነን መሪዎች አገልጋይ መሆን የሚቸግረን ጉዳይ ባይሆንም፥ ስለ ሀገራችን ጉዳይ ግን ያለውን ሁኔታ መግለፅ ከትግል ግዴታዎቻችን አንዱ በመሆኑ በአርምሞ የምናልፈው ሊሆን አይችልም።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ድምፅ፥ አምባገነንና አሸባሪ ቡድን ብሎ ፈርጆ የሚታገለውን የወያኔን ዘረኛ ድርጅት፥ ምዕራባውያን ለራሳቸው ጥቅም አስጠባቂ አገልጋይ አድረገው የሚያስታጥቁትን ቡድን ለምን እንደ

ምንቃወመውና እንደምንታገለው በትክክል ሊያውቁት ይገባል። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈፀመውና በሌላው ዓለም የሚካሄደው የአሸባሪ ተግባር የተለያየ ትርጉም ይሰጠዋል ካልተባለ በስተቀር፥ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በብሔር ስም ተደራጅቶ ሥልጣን ላይ በመጣ ዘረኛ ቡድን በመላው የሀገሪቱ ሕዝብ ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ መንግሥታዊ ሽብርተኝነት በመካሄድ ላይ ነው። የወያኔ ቡድን የምዕራባውያኑ ተባባሪያቸው በመሆኑ፥ ለመቀበል ባይፈልጉም፥ በሀገራችን የሚፈፀመው ሽብርተኝነት ዓለም ያወቀው፥ ፀሀይ የሞቀው የማይታበል ሐቅ ነው።ይህ በጠበንጃ ኃይል የመጣ ቡድን በአንድ ሀገር ሕዝብ ላይ የሚፈፅመው ግልፅና ስውር የጅምላ ጭፍጨፋ አሸባሪ ካላሰኘው፥ አሸባሪ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ምዕራባውያን ተባባሪዎቹ የሽብርተኝነትን ትክክለኛ ትርጉም ሊገልፁ ይገደዳሉ። ትላንት በሥልጣኔ ስም በዓለም ላይ ከፍተኛ ግፍ ተፈፀመ እይተባለ ሲለቀስ፥ ዛሬ ደግሞ በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በሀገር በቀል አሸባሪ ድርጅት መሪዎች ጭካኔ የሚደረገውን ጭፍጨፋ ስንመለከት፥ ይህች ዓለም ምንኛ የፈሪሳውያን መቀለጃ መሆኗን እንረዳለን። የምዕራባውያን የተለያዩ አቫይ ሚዛኖችና መስፈሪያዎች በሦስተኛው ዓለም ተብሎ በሚጠራው ክፍለ ዓለም በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ የሚያደርጉትን ቀልድ ተገንዝቦ ከአሁኑ አስፈላጊውን የመከላከያ ዘዴ ማዘጋጀት ካልተቻለ፥ ነግ ከነገ ወዲያ በስፋትና በጥልቅ የሚመጣውን ዘመናዊ የእጅ አዙር የቅኝ አገዛዝ ጥቃት መቋቋም የሚቻል አይመስለንም። ምናልባት ነገ የሚመጣውን የመከራ አደጋ ለመከላከል በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የቀድሚያ አጀንዳው ላይሆን ይችል ይሆናል ብለን ብንፅናናም እንኳ "መጀመሪያ የመቀመጫየን" አለች እንደሚባለው ይትበኃል መጀመሪያ ሀገራችንን ከጥፋት ማዳን መሆኑን እንረዳለን። በመሆኑም የኛ ወቅታዊውና አንገብጋቢው ጉዳይ የራስችንን ጠላት የሆነውን የወያኔ አሸባሪ ድርጅት ማስወገድ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም።

ዛሬ ምዕራባውያን ለራሳቸው የግል ጥቅም ጠበቂና ተከላካይ አድርገው የሚጠቀሙበትን ወያኔ በጊዚያዊ ደረጃ ቢገለገሉበትም፥ ከረዠሙ አኳያ ሲታይ ግን የመላውን ኢትዮጵያን ሕዝብ ወዳጅነት እያጡ መሄዳቸውን ሊገነዘቡት በተገባ ነበር።ይህንን ደግሞ ያደርጉታል አይባልም።አይጠበቁምም። ምክንያቱም፥ ከዓለም አቀፍ ፖለቲካና የዲብሎማቲክ ዘይቤያቸው ጋር የሚስማማ ስለአልሆነ ነው። ታዲያ ብልህ ዲፕሎማሲ መሠረት የሚያደረገው የአንድን ሀገር ዘለቄታዊ ጥቅም እስከሆነ ድረስ፥ ለምዕራባውያኑ፥ የዘለቂታ ብሔራዊ ጥቅም ሚዘን የደፋ ወደጅነት ሊያተርፍላቸው የሚችለው 77 ሚሊዮን ከሆነው ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መወዳጀት እንጅ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀንደኛ ጠላት ከሆነው ብሎም፥አላፊ-ጠፊ ከሆነውና ወደጅነቱ ዕፍ ሲሉት ጭልት ከሚሆነው ከወያኔ ጋር መሆን አይገባውም ነበር። ወጤት የሚያመጣ ፖለቲካ ለመጫዎት ከተፈለገ፥ በጊዚያዊ አፍለኛ ዲፕሎማሲ ቀለበት ውስጥ ገብቶ መተብተብ ለዘለቂታ ሀገራዊ ጥቅም የሚያስገኘው ውጤትአውንታዊ ሊሆን እንደማይችል በዕርግጠኝነት ከመናገር ልንገታ አይገባንም።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በታሪኳ፥በሥልጣኔ ስም በዕዳን ወረዋታል፥አጥቅተዋታል። በሃይማኖትም ስም ሌሎች ጎድተዋታል። ህልውናዋን ተፈታትነውታል። ቅርሷንና ታሪካዊ ኃብቷን ብዘብዘውታል። ገዳማቷንና የታሪክ መካናትን አጠፋፍተውባታል። ይህ ሂደት ደግሞ፥ በተደጋጋሚና በተፈራራቂ የታሪክ አጋጣሚዎች ኢትዮጵያ ሀገራችንን ኅልውናዋን ሊፈታተን እስከሚችል ጠርዝ አድርሷታል። የዛሪይቱ ኢትዮጵያ በበኩሏ የአለም አቀፍን አሸባሪነት ለመከላከል በሚል ሳብያ የአሸባሪውን የወያኔ መንግሥት አባሪ ተባባሪ አድርገው በሚያዝዙት የውጭ ባዕዳን አማካኝነት የዚህ ክስተት ሰለባ ልትሆን በቅታለች። ትላንት ኦ! ሥልጣኔ በስምሽ ስንት ግፍ ተፈፀመ? ኦ! ዴሞክራሲ በስምሽ ምን ያህል ወንጀሎች ተካሂዱብሽ? እንዳልተባለ ሁሉ፥ ዛሬ ደግሞ ኢትዮጵያ ሀገራችን ኦ! ኢትዮጵያ በሰላምና ፀጥታ ስም ምን ያህል የአሸባሪዎች ሰለባ ሆንሽ እየተባለች ትገኛለች። /////----